## “የትውልዱ ትውስታ”… ውቅያኖስን በጭልፋ

## በኦስሎ በአቶ አሊ ሰኢድ ስለቀረበው ፊልም አስተያየት፣

ከያሬድ ተሾመ

ድሮ በዛፍ ጥላ ሥር ሙግት ወግ የቻለ ባለ አፈ-ሊቅ ነበር አሉ የሚረታው፡፡ በኩታ አጣጣልህ፣ በግር አሰዳደርህ፣ በእጅና ከዘራ አሰነዛዘርህ ካላማረብህ በችሎቱ ተረታህ ማለት ነው፡፡ “በልሀ-ለበልሀ” ብለህ ቀድመህ ሰዩመ ችሎቱን ካላወደስክ፣ ከወገብህ እንድሚገባ ካላጎነበስክ፣ የምታስገባውን ግብር ካሳነስክ መረታት ብቻ አይደለም አልፎም መታሰር ሊገጥምህ ይችል ነበር አሉ። የተቀማኸውን ሞፈር፣ የተዘረፍከውን ከብት፣ የተቃጠለብህን ውድማ ወዘተ… ባይንህ እያየህ ለባላጋራህ ሊፈረድ ይችላል… ድንቄም ችሎት። ይህ ብቻ አይደለም የጌቶችና የሜቴ ከብቶች ውሀ ሳይጠጡ ቀድሞ ያደፈረሰ፣ በቅጥራቸው ዙሪያ ማገዶ የሰበረ፣ ግብር ሳያስገባ ልጁን ያጎረሰ ወዘተ… ጥሩ ተናጋሪም ቢሆን የትም አያመልጥ፡
በወንጀሉ ላይ “ንጉስ ይተነፍሳልና..” ከመገደል ከተረፍክ ዘብጥያ ትቀያለህ።

ሰሞኑን በመዲናችን ኦስሎ በአቶ አሊ ሰኢድ ሕይወትና በትግል ጓዶቹ ዙሪያ የሚያጠነጥነውና በካናዳዊው አዘጋጅ አሮን ፍሎረሰኮ የተዘጋጀውን ድክመንተሪ ፊልም ተመለከትኩና ጥቂት ነገሮችን ለማለት ወደድኩ።

የዛሬው አቶ አሊ ጥንት ገና ከእናታቸው እግር ስር በመንደራቸው ድክ ድክ እያሉ ባሉበት ወቅት ከእናታቸው ጋር ኑሯቸውን ለማሸነፍ ማገዶ ሰበራ ግድ ይል ኖሮ ተያይዘው ሲወጡ ሳለ ድንገት በ”ነሜቴ” አጥር ዙሪያ የወደቀ ጭራሮ ለቅመው ኖሮ ያለ ችሎት በዚያ ጨቅላ ዕድሜያቸውየማይችሉትን የስቃይ ልምምድ ይያያዙታል። ታዲያማ በዚህ የጀመረው ሕይወት የጅማሬ ሂደቱ በእጅጉ ለማየት ቀርቶ ለማሰብ የሚከብድ ነበር።

ለዛ ባለው የትረካ ዘዴያቸው “ሕይወት” እንድዚያው ቀጠለ እያሉ ከማጡ ወደ ድጡ ሲያሻግሩን የ አሥራ አንድ እስር ቤት ቆይታ ታሪካቸውን ሲያወጉን የደርግን ጭካኔ፣ የቀይ ሽብርን መከራና ስቃይ፣ የሱማሌ ስደታቸውንና የእስር ቤት ቆይታቸውን ሲያወጉንና ሲያሳዩን  የትግል ጓዶቻቸውን ስም ያለምንም ችግር እያስታወሱ ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታውን ሲያወጉን በትውስታ ክህሎታቸው፣ በልጅነት አእምሯቸው ውስጥ የገቡበት የዓላማ ጽናትና የውሳኔ ጥብቀት እጅግ እየተገረምን አየን .. “ሕይወት እንድዚያው ቀጠለ” እያሉ ከዚህኛው እስር ቤት ተፈታሁ ብለው ለጊዜው ያረፍን ሲመስለን፡ “ለኛ ከእስር መፈታት ደስ አይልም” እያሉ መልሰው መልሰው እያሰሩ ይከቱናል። አብሮ የሚቀር ዓላማ፣ አብሮ የሚቀር ትግልና የትግል ጓድ አለና መፈታቱ ዋጋ የለውም ብለው መልሰው ያስሩናል፡ … ምን ይሄ ብቻ የሱማሌ የስደት ሕይወት መከራቸውን ጨርሰው በካናዳ የነፃ ጎዳና ላይ እየወሰዱን እንኳን እዛው ያስሩናል። ፈገግ እያደረጉ ያስሩናል። በየ እስር ቤቱ ሲገርፋቸውና ሲያሰራቸው የሚያውቁት ፊት “እዚህም እንዴት መጣህ?” እዚህም ጥበቃ ነኝ አለኝ እያሉን እንደገና የካናዳ የትግል ሕይወታቸውን ያወጉናል።

እንዲህ እንዲህ እያሉን ምናልባትም በትግል ጽናት በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያዋ ሊሆኑ የሚችሉቱ የ94 ዓመት እናታቸው በጠራና ኩልል ባለ አገላለፅ ዛሬም ከልጃቸው ጋር የትግል ክንዳቸውን ሲዘረጉላቸው አንድም ከአብራካቸው እንደወጣ ልጃቸው የእናት ፍቅራቸውን ሌላም እንደ ጀግናና ፅኑ የትግል ጓዱ ሆነው ሲያበረታቱት እናያለን። ግሩም እናት።

እንደው ዕድሉን አግኝተን ፊልሙን ላላየነው ገርደፍ አድርጌ ልንገራችሁ ብዬ እንጂ ቢዘረዘር ዝርዝሩ ጥልቅ ነው። አንድ ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ አካባቢ የፈጀው ይኸው ፊልም ታዳሚውን በዝምታ ድባብ ይዞ ስሜቱን ወጥሮት ነበር የቆየው ፊልሙ እስከሚጠናቀቅ “የትውልዱ ሕይወት” ይመስል ነበር ርዕሱ … እየኖረ ነበር የተመለከተውና።

ለዚህም እንደ አብነት የፊልሙ ባለታሪክ አቶ አሊ ለትግሉ ወስነው ሲሰደዱና ጭቅላ ልጆቻቸውን በተኙበት እንዴት እንደተሰናበቱ ሲገልፁ በአዳራሹ ሳግ ይደመጥ ነበር፡"... አንገታቸው ስር ገብቼ ጠረናቸውን ስነቅሁ ... ልክ ልጇን እንደምትልስ እናት ላም ገላቸውን እያገላበጥኩ ላስኳቸው ..." እያሉ ሲያወጉን ትግል የሚያስከፍለውን ዋጋ የተመኑን ክብደት እያሰብን አነባን።

ታዲያ ደግሞ ጥቂት እንድናርፍም ሲሹ ያኔ ከሱማሌ ስደት በኋላ ወደ ካናዳ እንደገቡ በካናዳ አንገት አይደፋም ዓይን ለዓይን እየታየ ነው የሚወራው ተብለው ኖሮ ስራ ፍለጋ ሄደው በገጠማቸው ቃለ መጠይቅ ላይ እንዴት እያፈጠጡ እንደመለሱ ሲያሳዩን! እንዲሁም የቀድሙ የደርግ ደብዳቢና ገራፊያቸው በካናዳ ምድር ላይ የዘበኛ ልብሱን ለብሶ "ስኩሪቲ" ነኝ ቢላቸው የተሰማቸውን ፍርሀትና ስሜት ደግሞ እያስፈገገ ይመልሰን ነበር። ... ትርጉም የሚሰጥ ፈገግታ።

ጥንታዊው የግሪክ ፈላስፋና የኪነ-ጥበቡ ባለሞያ አሪስቶትል ጥበብን ይታደሷል እንጅ አይታገሉትም እንዳለው አቶ አሊ ጥበብ ታድሷቸው መወለዳቸው ድርድር ውስጥ የምናስገባው ጉዳይ አይደለም። እናም ከፊልሙ ጋር በአጋጣሚው ባለታሪኩን ራሳቸውን ማግኘታችን ይበልጥ ትውስታውን ምሉዕ አድርጎልን ነበር የዋለው።

የእንካ-ስላንቲያ ወጋቸው፣ ያለ ወረቀት ከአንደበታቸው የሚፈሰው ስነ-ግጥማቸውና መነባንባቸው፣ ቀልዶቻቸውና የገጠመኝ ትረካዎቻቸው በእጅጉ የሚማርኩና ታዳሚውን ለደቂቃ ሌላ ነገር እንዳያስብ የሚያደርጉ ናቸው፡ የድሮ-ስነቃል (oral literaure) ወጎቻችን፣ በሀዘንና በደስታ፣ በየሥራ ቦታችንና በየዓውደ በዓሎቻችን እያንጎራጎርን የምንጠቀምባቸው የነበሩትና ለትውልድ መቆየት የነበረባቸው ቢሆንም ቅሉ እየደበዘዙብን ያሉትን ትውፊቶች በእርሳቸው ትንሳኤ ያገኙ ይመስሉ ነበር ... ይፈልቃሉ። አስገራሚ የኪነ-ጥበብ ሰውም ናቸው፡ ሕይወትን በኪነ-ጥበብ ቃና እየከሸኑ የሚኖሩ ባለሞያ። በፊልማቸው ላይ ትንሽ አቅምሰው እንዳንቆዝም እያጓጉን ይተውታል እንጅ ጣቶቻቸው እንኳን እስር ቤት የሚደረድሩት የነበሩትን የክራር ጅማቶች ላይ ሲሮጡ ቀልብን የሚይዙ ነበሩ።

በተለይም እ.ኤ.አ. ከ18 መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ የተነሱት የሪያሊዝም ትያትር ባለሙያዎች ትያትር በአራት ግድግዳ ስምምነት (4th wall convention) ከተመልካቹ ጋር የመስማማት ውጤት ነው በማለት ተመልካቹ ተደብቀን የምንኖረውን ሕይወት ተደብቆ እንደሚያይ መሆን አለበት በማለት ይስማሙ ነበር። አቶ አሊ ይህንን የሪያሊዝምን ጥበብ ሕግ በሚገርም ሁኔታ ለውጠውታል። ተመልካቹን በእንካ-ስላንትያ እየጠየቁ በመልሱ እየተቀኙ ሲጫዋወቱ መድረክ የመቆጣጠር ችሎታቸው የሚገርም ነበር።

"የትውልዱ ትውስታ" ዶክመንተሪ ፊልም ሆነና ከሚነሳበት እውነተኛ ታሪክ ላይ ዝንፍ ሳይልና የታሪክ ፈጠራ ሳይጨምር በተገኘው መረጃ ተረከው እንጅ እንደ ክህሎቱ ብዙ ሊያደርገው እንደሚችል መገመት ይቻል ነበር። በእርግጥ ነው በነ አቶ አሊ ጊዜ የነበረው ያ ትውልድ እያንዳንዱ የትግል ጓዶች ቢተርኩት ኖሮ ፈጠራና እውነትነቱን ለመለየት እስከምያዳግተን ድረስ እንደምንደነቅ ግልጽ ነው አቶ አሊ ራሳቸው በመግቢያቸው "የትውልዱ ትውስታ" ጠቅላላ ትግሉን በጭራሽ አይወክልም ይልቁኑም ከበዛው ፀጉራችን አንዷቷን የመምዘዝ ያህል ነው በማለት የገለፁት። ውቅያኖስን በጭልፋ።

እንደተባለው የዶክመንተሪ ፊልም ባህሪ ከሚጠይቀው መሠረታዊ አለባውያን ዋነኛው እውነተኛነትና ታማኝነት መሆኑ፣ የምንጬቻቸው ባለቤትነት መብታቸውና ህጋዊነታቸው፣ የባለታሪኮቹ ፈቃደኝነት ወዘተ...እንደተፈለገው አለመካተታቸው በመጠኑም ቢሆን የተሻለ ብቃቱን እንደገቱት መናገሩም ተገቢ ነው።

ፊልሙ በመረጃ መሰባሰቡና በስራ ቆይታው ከአራት ዓመታት በላይ የፈጀና ከ750 ያላነሱ ፎቶዎችን ያካተተ መሆኑ ድካሙ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም ይህ ቢሆንም ትረካውን ከዚህ ባለፈ ሊያግዙ የሚችሉ ከፎቶዎች የበለጠ ወደ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ላይ ያተኮረ ቢሆን ኖሮ እንዴት ግሩም በነበር ነበር። የመረጃ ማግኘቱ ጥረት እንዲህ እንዲሆን ያስገደደው ቢሆን እንኳን በጥቂቱ እንደተሞከረው የሌሎች ተጨማሪ ተናጋሪ አብነቶችና ዕውነቱን የጠበቀ ረዘም ያሉ የትወና እገዛዎች ቢኖሩበት እንደ ሌላ አማራጭ በሆነ ነበር።

"የትውልዱ ትውስታ" ቀጣይ ክፍል በርካታ ተጨማሪ ነገሮችን አካቶ እንደሚመጣ በራሳቸው በአቶ አሊ የተጠቆምን መሆኑን ስናውቅ ደግሞ እዚህ የጎደሉት በቀጣዩ እንደሚሞሉ ተስፋ እንድናደርግ ግድ አለን።

በመጨረሻም አቶ አሊ ስለፊልማቸው እሴት የተናገሩትን አንስቼ እኔም ነገሬን ልቋጭ “የፊልሙ ዓላማ ቂም መቋጠሪያና ቁርሾ ማስንበቻ አይደለም ይልቁንም ለትውልዱ እጅግ ሰፊ ከሆነው የሦስት” መንግስት የጭቆና ታሪክ ቁንጽሏን እንኳ በታሪክ ማጎደርነት ለተተኪው ትውልድ ማቆየት ነው..”

“አነሳሾቼ ልጆቼ ናቸው በቤተሰብ ጨዋታችን የትግል ታሪኬን ዘወትር ስተርክላቸው ታሪኩን በመውደዳቸው አንተ ስታልፍ ያበቃል እያሉ አስፈራሩኝ... እናም ትውስታውን አቆየው ዘንድ ማስፈራሪያቸው መነሻዬ ሆነኝ። ”

ግሩም ቤተሰብ ከልጅ እስከ አያት።